በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በገቢዎች ሚኒስቴር
የጉምሩክ ኮሚሽን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues
Customs Commission

ቀን 09 ታህሳስ 2011
Date
ቁጥር 4.0/201/11
Ref. No.

የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት፣

ጉዳዩ፡- በተወሰኑ ክልሎች በጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ ፍጆታ የሚያገለግሉ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ፈቃድ የተሰጠበት መመሪያ ተፈፃሚነት እንዲቋረጥ የተላለፈውን ውሳኔ ይመለከታል።

በኦሮሚያ፣ በሱማሌ እና በአፋር ክልሎች በሚገኙ የተወሰኑ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍጆታ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ ቁጥር 40/2007 (ከነማሻሻያዎቹ) እንዲቋረጥ የተወሰነ መሆኑን ህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በቁጥር ገ/አ/1/2/286 ከገንዘብ ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት ተሰጥቶ የነበረዉ መብት ከህዳር 19 ቀን 2011 እንዲቋረጥ ኮሚሽኑ በቁጥር 4.0/143/11 ህዳር 24 ቀን 2011 ዓ/ም ማሳወቁ ይታወሳል። ሆኖም ከላይ ቀንና ቁጥሩ የተጠቀሰው ውሳኔ ለክልል ንግድ ቢሮዎችና ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እስኪደርስ ድረስ በሂደት ላይ የነበሩ ዕቃዎች በመኖራቸው አቤቱታዎች የቀረቡ ስለሆነ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

1. ዕቃዎች ተጓጉዘው ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የደረሱ፣
2. የትራንዚት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ አገር ውስጥ በማግባት ላይ ያሉ፣
3. በተፈቀደላቸው ኮታ መሠረት ከሚመለከታቸዉ የክልል ንግድ ቢሮዎች ክሊራንስ ተሰጥቷቸው እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ቀርበው የትራንዚት ፈቃድ የሚያገኙ የመብቱ ባለቤቶች በነበረው አሰራር እንዲስተናገዱ እና

ከጥር 01 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/286 ህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በተወሰነው መሠረት ተሰጥቶ የነበረው የፍራንኮ ቫሉታ መብት መቋረጥ ተግባራዊ እንዲደረግ በቁጥር ገ/ኢ/1/2/291 በቀን 08/04/2011 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል።





☎ +251 115 62 ...
+251 115 62 ...
✉ 2559
Addis Ababa, Ethiopia

ስለሆነም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ተፈፃሚ እንዲደረግ እያሳወቅን፤ ከውሳኔው አግባብ ውጭ ማንኛውም ዓይነት ህገ-ወጥ ተግባር ህጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን በመገንዘብ አፈፃፀሙ ላይ የተሟላ ጥንቃቄ እንዲደረግ በጥብቅ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብሴ ብታ ሁርሳ
ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

* በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ኮሚሽን * The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues Customs Commission

ግልባጭ:-

- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለገንዘብ ሚኒስቴር

  አዲስ አበባ፣

- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድ ቢሮ
- ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ ቢሮ
- ለሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ ቢሮ

  ባሉበት፣

- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

  ጉምሩክ ኮሚሽን፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር 7/ኢ/1/2/291
ቀን 8/4/2011

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>፣

በተወሰኑ ክልሎች በጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ ፍጆታ የሚያገለግሉ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ፈቃድ የተሰጠበት መመሪያ ተፈፃሚነት እንዲቋረጥ የተላለፈውን ውሳኔ ይመለከታል።

በኦሮሚያ፣ በሱማሌ እና በአፋር ክልሎች በሚገኙ የተወሰኑ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍጆታ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ ቁጥር 40/2007 (ከነማሻሻያዎቹ) እንዲቋረጥ የተወሰነ መሆኑን ህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በቁጥር ገ/ኢ/1/2/286 በተፃፈ ደብዳቤ ማሳወቃችን ይታወሳል። ሆኖም ከላይ ቀንና ቁጥሩ የተጠቀሰው ውሳኔ ለአስፈፃሚ አካላት እስኪደርስ ድረስ በሂደት ላይ የነበሩ ዕቃዎች በመኖራቸው አቤቱታዎች የቀረቡ ስለሆነ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ከታች የተዘረዘሩ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ፡-

1. ዕቃዎች ተጓጉዘው ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የደረሱ፣
2. የትራንዚት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ አገር ውስጥ በመግባት ላይ ያሉ፣
3. በተፈቀደላቸው ኮታ መሠረት ከሚመለከታቸዉ ክልል ንግድ ቢሮዎች ክሊራንስ ተሰጥቷቸው እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ቀርበው የትራንዚት ፈቃድ የሚያገኙ የመብቱ ባለቤቶች በነበረው አሰራር እንዲስተናገዱ ሆኖ ከጥር 01 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/286 ህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በተወሰነው መሠረት ተሰጥቶ የነበረው የፍራንኮ ቫሉታ መብት መቋረጥ ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ
ሚኒስትር ዲኤታ

<u>ግልባጭ</u>፡-
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
- ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
- ለሶማሌ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
<u>በያሉበት</u>፣

ጉዳ|101
03/04/11

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በገቢዎች ሚኒስቴር
የጉምሩክ ኮሚሽን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues
Customs Commission

ቀን 24 ህዳር 2011
Date
ቁጥር 4-0/143/11
Ref. No.

ለየጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት፣

ጉዳዩ፡- በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች በሚገኙ አንድ አንድ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቆም መወሰኑን ስለማሳወቅ፣

በጠረፍ አካባቢዎች የመሠረተ ልማት ውስንነት የሚፈጥረውን የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት አቅርቦት እጥረት ችግር ለማቃለልና በእነዚህ አካባቢዎች ነዋሪ የሆነው ህበረተሰብ እነዚህን መሠረታዊ አቅርቦቶች በአነስተኛ ዋጋ ሸምቶ እንዲጠቀም ለማስቻል፣ የህገ-ወጥ ንግድ ተፅዕኖን ለማስወገድ በማሰብ በአገራችን በአንድ አንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የሚያገለግሉ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ከውጭ እንዲገቡ የሚፈቅድ መመሪያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም. እንዲሁም ይህንኑ መመሪያ የሚያሻሽሉ መመሪያዎች ግንቦት 01 ቀን 2007 ዓ.ም. እና መስከረም 15 ቀን 2009 ዓ.ም. ማስተላለፉን በመግለፅ እና መመሪያው የታሰበለትን ዓላማ በማሳካት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ ህገ-ወጥ ንግድን በማስፋፋት በአገር ውስጥ የንግድ ውድድር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረና ለውጭ ምንዛሪ ጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት መሆኑን በመግለፅ በመመሪያው የተፈቀደውን የቀረጥና ታክስ ልዩ መብት ማንሳት ተገቢ መሆኑን እና እንዲሁም ይህ መመሪያ ከተላለፈበት ቀን በፊት ወደ አገር ውስጥ ለመግባት በመንገድ ላይ ያሉ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳትን ሳይጨምር ከህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች ለሚገኙ የተወሰኑ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍጆታ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበትን መመሪያ ቁጥር 40/2007 (ከነማሻሻያዎቹ) በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቋረጥ የተወሰነ ስለመሆኑ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቁጥር 7/ኢ/1/2/286 በቀን 19/03/2011 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል። 

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!!

☎ +251 115 62 93 00
Fax +251 115 62 93 19
✉ 2559
Addis Ababa, Ethiopia

በዚሁ መሠረት መመሪያው ከተላለፈበት ከህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ ውሳኔው ተፈፃሚ እንዲሆን አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues Customs Commission

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ፡-

- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለገንዘብና ሚኒስቴር
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድ ቢሮ
- ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ ቢሮ
- ለሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ ቢሮ

  በያሉበት፣

- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ

  ጉምሩክ ኮሚሽን፣

አስቸኳይ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር
Ref.No. 7/ኢ/1/2/286
ቀን
Date 19/3/2011

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

በጉዳዩ፡- በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች በሚገኙ አንድ አንድ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ <u>በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቆም መወሰኑን ስለማሳወቅ፣</u>

በጠረፍ አካባቢዎች የመሰረተ ልማት ውስንነት የሚፈጥረውን የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት አቅርቦት እጥረት ችግር ለማቃለልና በእነዚህ አካባቢዎች ነዋሪ የሆነው ህብረተሰብ እነዚህን መሰረታዊ አቅርቦቶች በአነስተኛ ዋጋ ሸምቶ እንዲጠቀም ለማስቻል፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ወደአገር ውስጥ በሚገቡ ደረጃቸውን ባልጠበቁ የምግብ ምርቶች ምክንያት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የጤና ችግር ለመከላከል እና በጠረፍ አካባቢ ያለውን የሕገ-ወጥ ንግድ ተፅህኖን ለማስወገድ በማሰብ በአገራችን በአንድ አንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የሚያገለግሉ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ከውጭ እንዲገቡ የሚፈቅድ መመሪያ መ/ቤታችን ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም እንዲሁም ይህንኑ መመሪያ የሚያሻሽሉ መመሪያዎች ግንቦት 1 ቀን 2007 ዓ.ም እና መስከረም 15 ቀን 2009 ዓ.ም ማስተላለፉ ይታወቃል።

መመሪያው የታሰበበትን ዓላማ እያሳካ መሆኑን ለማረጋገጥ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ከንግድ ሚኒስቴር የተውጣጣ የጥናት ቡድን ተቋቁሞ ቡድኑ የፈቃዱ ተጠቃሚ በሆኑ ክልሎች በሚገኙ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ከሆነው ህብረተሰብ፣ ከአቅራቢዎችና ከቸርቻሪ ነጋዴዎች ጋር ውይይት በማድረግ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ከየክልሉ የንግድ ቢሮዎች፣ ከንግድ ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መረጃዎችን በመሰብሰብ የመመሪያውን አፈፃፀም መገምገም የሚያስችል ጥናት አካሄዷል። በተደረገው ጥናት መንግሥት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲባል ከቀረጥና ታክስ ሊሰበስብ ይችል የነበረውን ከፍተኛ ገቢ ሳይሰበስብ ቢቀርም ህብረተሰቡ በአቅርቦትና በዋጋ ረገድ በአግባቡ ተጠቃሚ አለመሆኑን፣ ስርዓቱ እንደተጠበቀው የኮንትሮባንድ ንግድን ከመከላከል ይልቅ ለሕገ -ወጥ ንግድ አመቺ ሁኔታን በመፍጠር ፍትሐዊ ያልሆነ የገበያ ውድድር እንዲኖር በማድረግ በአገር ውስጥ አምራቾች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማስከተሉን፣ ለውጭ ምንዛሪ የጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት በመሆን በሕጋዊ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ውጤት እያስከተለ መሆኑን፣ የመመሪያው አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተጠበቀው ደረጃ አለመሆኑን፣ ከፍትሐዊ ተጠቃሚነት አኳያ መመሪያውን የጠረፍ አካባቢዎች ባሉባቸው ክልሎች ሁሉ ተፈፃሚ ማድረግ ተገቢ ቢሆንም ይህንን ማድረግ በአገሪቱ የንግድ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን እንዲሁም በመመሪያው የተዘረጋው ሥርዓት በጎረቤት

Letter/Hb/ Ta

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa- Ethiopia
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር Ref.No 7/ሺ1/2/286
ቀን Date 19/3/2011

አገሮች መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ተግባራዊ የሚደረገውን የድንበር ንግድ አሠራርን የማይተካ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

በፍራንኮ ቫሉታ ቀረጥና ታክስ ነፃ መመሪያ ቁጥር 40/2007 አንቀጽ 8 የተፈቀደው የቀረጥና ታክስ ልዩ መብት ለሕዝብ የተፈለገውን ጥቅም የማያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ መብቱ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ እንደሚችል ተደንግጓል። በተደረገው ጥናት መመሪያው የታሰበለትን ዓላማ በማሳካት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ ሕገ-ወጥ ንግድን በማስፋፋት በአገር ውስጥ የንግድ ውድድር ላይ አሉታዊ ተጽህኖ እያሳደረና ለውጭ ምንዛሪ ጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ በመሆኑ በመመሪያው የተፈቀደውን የቀረጥና ታክስ ልዩ መብት ማንሳት ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል።

ስለዚህ ይህ መመሪያ ከተላለፈበት ቀን በፊት ወደ አገር ውስጥ ለመግባት በመንገድ ላይ ያሉ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳትን ሳይጨምር ከህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች ለሚገኙ የተወሰኑ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍጆታ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ ቁጥር 40/2007 (ከነማሻሻያዎቹ) በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቋረጥ የተወሰነ መሆኑን አስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለጉምሩክ ኮሚሽን
- ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- አዲስ አበባ

Letter/Hb/TA

ስልክ Tel 251-11-155 24 00, 22 66 93
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa- Ethiopia
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ